# BBC LEARNING ENGLISH
# Essential English Conversation
## At the restaurant
## ምግብ ቤት ውስጥ

*This is not a word-for-word transcript*

**ዘሩባቤል**
ጤና ይስጥልን። ማንኛውም የእንግሊዝኛ ተማሪ ሊያውቃቸው የሚገባ የቋንቋ መሰረታዊያንን ወደሚያቀርበው Essential English Conversation እንኳን በደህና መጡ። ዘሩባቤል እባላለሁ። በዚህ ክፍል ምግብ ቤት ገብተው ምግብ ማዘዝ የሚችሉበትን ቋንቋ ይማራሉ።
አንድ ተጠቃሚ ምግብ ቤት ውስጥ ምግብ ሲያዝ ያዳምጡ።

***Phil***
*How can I help you?*

***Sian***
*Hi, can I have the meat stew? And some water to drink.*

***Phil***
*Yes, of course.*

**ዘሩባቤል**
ይህ አስቸጋሪ ቢሆንብዎት ብዙም ጭንቀት አይግባዎት፤ ውይይቱን ከፋፍለን እንዲለማመዱት እናግዝዎታለን።
አስተናጋጁ ተጠቃሚዋን ምን ልርዳዎት 'How can I help you?' ሲል ጠይቋታል። ይህ ሰዎች ሱቆች፤ ምግብ ቤቶች እና ገበያ ውስጥ ምን እንደምትፈልጉ ለመጠየቅ የሚሉት ነገር ነው። ያዳምጡና ደግመው ይበሉ።

*How can I help you?*

**ዘሩባቤል**
ከዚያም ደንበኛዋ ስጋ 'meat' እና ስጎ 'stew' እንደምትፈልግ ገልፃለች። ጥያቄ ለማቅረብም፥ 'Can I have…? የሚለውን ሀረግ ተጠቅማለች።

*Hi, can I have the meat stew?*

**ዘሩባቤል**
ደንበኛዋ በተጨማሪም ለመጠጥ 'drink' የሚሆን ውሃ 'water' ጠይቃለች።

*And some water to drink.*

**ዘሩባቤል**
አስተናጋጁ 'Yes, of course' እሺ፤ በሚገባ' ብሏል። ያዳምጡና ደግመው ይበሉ።


© British Broadcasting Corporation 2018

*Yes, of course.*

**ዘሩባቤል**
በጣም ጥሩ፤ ያሉትን ለመፈተሽ የተለያዩ ሰዎች ምግብ ቤት ውስጥ ምግብ ሲያዙ ያዳምጡ።
ስቴፋኒ ያዘዘችው 'vegetable' አትክልት፥ 'stew' ስጎ እና 'juice' ጭማቂ ነው።

*How can I help you?*

*Hi, can I have the vegetable stew? And some juice to drink.*

*Yes, of course.*

ክሪስ የፈለገው ዓሣ 'fish' እና ለስላሳ 'soda' ነው።

*How can I help you?*

*Hi, can I have the fish? And some soda to drink.*

*Yes, of course.*

**ዘሩባቤል**
እሺ፤ አሁን ደግመን እንሞክረው። የእንግሊዝኛ አረፍተ ነገሮቹን ያዳምጡና ደግመው ይበሉ። እያንዳንዳቸውን ሁለት ሁለት ጊዜ ይሰማሉ።

*How can I help you?*
*How can I help you?*

*Hi, can I have the meat stew?*
*Hi, can I have the meat stew?*

*And some water to drink.*
*And some water to drink.*

*Yes, of course.*
*Yes, of course.*

**ዘሩባቤል**
በጣም ጥሩ! እንግሊዝኛውን ምን ያህል እንደሚያስታውሱት እንይ። አረፍተ ነገሮቹን በአማርኛ ያዳምጡና የእንግሊዝኛ አቻቸውን ይበሉ።
*ምን ልርዳዎት?*
*How can I help you?*

*የስጋ ወጥ ማግኘት እችላለሁ?*
*Hi, can I have the meat stew?*

*እና የሚጠጣ ውሃ*
*And some water to drink.*

*እሺ፥ በሚገባ።*
*Yes, of course.*

**ዘሩባቤል**
ግሩም! አሁን ምግብ ቤት ገብተው ምግብ በእንግሊዝኛ እንዴት ማዘዝ እንደሚችሉ ያውቃሉ። ለሲያን ምላሽ በመስጠትና የሚፈልጉትን በመናገር ይለማመዱ።

*How can I help you?*
*Yes, of course.*

**ዘሩባቤል**
አሁን መልስዎን ለማመሳሰል ሙሉውን ውይይት ያዳምጡ።

***Phil***
*How can I help you?*

***Sian***
*Hi, can I have the meat stew? And some water to drink.*

***Phil***
*Yes, of course.*

**ዘሩባቤል**
በጣም ጥሩ! አሁን ምግብ ቤት ገበተው በእንግሊዝኛ ቋንቋ ምግብ ማዘዝ ችለዋል። የተማሩትን መለማመድ አይዘንጉ። ጓደኛ ይፈልጉና በእንግሊዝኛ ምግብ በማዘዝ ይለማመዱ። ለተጨማሪ የዕለት ተዕለት እንግሊዝኛ በሚቀጥለው ዝግጅታችን ይጠብቁን።


© British Broadcasting Corporation 2018